# “የምንጩን ባለቤት ውሃ ነፈጉት”

# እስከመቼ?

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ከታደለቻቸው እጅግ በርካታ ሀብቶቿ መካከል አንዱ ውሀ ነው፡፡ በርካታ ሀይቆቻችን፣ ወንዞቻችን፣ ምንጮቻችን ወዘተ ለዚህ እውነት ተጨባጭ ማስረጃዎቻችን ናቸው፡፡ ለአብነት ያህልም የዓባይ ወንዝን አንስቶ ብዙ መነጋገር ይቻላል፡፡

የኢትዮጵያ የምሥራቅ አፍሪካ የውሀ ማማነት ታሪክ ዘመናትን ያስቆጠረና እድሜ ጠገብ ከመሆኑም  በላይ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረ ስለመሆኑ የዓባይ ወንዝ አንዱና ትልቁ ማረጋገጫ ነው፡፡  የዓባይ ጉዳይ ከኢትዮጵያም አልፎ የሱዳንና የግብፅ የሕልውናቸው መሠረት በመሆኑ አንድ እራሱን የቻለ ታላቅ አጀንዳ ነው፡፡ ስለአባይ ያሉ እውነታዎችን በርካታ ፀሀፍት ያረጋገጡት፣ አርቲስቶች ከበቂ በላይ የዘመሩት፣ የዓላማችን ፖለቲከኞች በስፋት የተነጋገሩበት፣ ባጠቃላይ ዓለም ያወቀው፣ ፀሀይ የሞቀው፣ ተፈጥሮአዊና ታሪካዊ እውነታዎችን በጉያው የያዘ በመሆኑ በሀገራችንም (በቂጭት) ብዙ ተፅፎለታል፤ ተገጥሞለታል፤ ተዘፍኖለታል፣ ተዘምሮለታል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፤ ለዘመናት አወያይቷል፤ አነጋግሯል፤ አመራምሯል፡፡ አሁንም እንደዚሁ፡፡

አባይ ከወንዝነቱ ባሻገር በከፍተኛ የውሀ መጠኑ፣ ማራኪ ፏፏቴዎቹ፣ አስገራሚ መልክዓምድራዊ አቀማመጡ፣ ለዓለም ሥልጣኔ ባበረከተውና እያበረከተ ባለው አስተዋፅኦ፣ አገርን ከሀገር ህዝቦችን ከህዝቦች ጋር ያስተሳሰረ የታሪክና የተፈጥሮ ሠንሠለት ነው፡፡

በተለይም በተፋሰሱ ግርጌ ለሚገኙ የአፍሪካ ሀገራትና ሕዝቦቻቸው የህልውና፣ በተፋሰሱ ራስጌ ለሚገኙ አገሮችም የልማትና የተጠቃሚነት ጉዳይ መሆኑ ከሌሎች ወንዞች ሁሉ ዓባይን ልዩና ፈርጀ ብዙ ያደርገዋል፤ ይህም የዓለምን ትኩረት የመሳብ ኃይሉን በእጅጉ ከፍ አድርጎታል፡፡

ትሩፋቱን የህልውናቸው እና የልማታቸው መሠረት ያደረጉት እነዚህ አገራት ከሌላው በተለየ መልኩ በዚሁ በዓባይ ወንዝ ላይ ያላቸው ትኩረት ከፍተኛ በመሆኑ ከዓይናቸው ብሌን የበለጠ ይሳሱለት ዘንድ እራሱ ዓባይ ግድ ብሏቸዋል፡፡ ዓባይ ማለትም ናይል ተብሎ የሚጠራው ወንዝ (ወንዛችን ማለቱ ይመረጣል) ከማህበራዊ፣ ኢኰኖሚያዊና ተፈጥሮአዊ ፋይዳው በዘለለ መልኩ ድንበር ዘለል ባህሪው ጠንካራ ፖለቲካዊ ይዘት እንዲኖረው አስገድዷል፡፡ በመሆኑም የዓባይ ጉዳይ (ስምምነት) እነዚህ በተፋሰሱ ራስጌና ግርጌ አካባቢ ለሚገኙ ሀገራት ፖለቲካዊ ይዘቱ በማመዘኑና እነሱን ከተጠቃሚነት ያገለለ በመሆኑ የተነሳ በ1991 ዓ.ም ‹‹ናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ›› የተሰኘ ተቋም ለመመስረት ተገደዱ፡፡ እነዚህ ሀገራት ለጋራ ተጠቃሚነት መሠረት ለመጣል አስፈላጊውን ሁሉ ሲያደርጉ መቆየታቸውን ባለፉት አሥርት ዓመታት ውስጥ በቅርብ የተመለከትነው አበረታችና ወቅታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡

ኢንሼትቩ ለምን አስፈለገ?

ለኢኒሼቲቪ እውን መሆን ከላይ የጠቀስናቸው የተፋሰሱ አካባቢዎች ሀገራትን በጋራ ፍቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የጋራ ስምምነትን ጠይቋል፡፡ ይህ ደግሞ በግንባር ቀደምትነት የውሃው ዋነኛ መገኛ የሆነችውን ኢትዮጵያንም አካትቷል፡፡

የናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭን ለመመሥረት ዋናውና መሠረታዊው ምክንያት በተደጋጋሚ ያጋጠመው የዝናብ ወቅት መዛባትና የሥርጭቱም አልፎ አልፎ መቀነስ በአካባቢው በግብርናው ዘርፍ በተሰማሩ ወገኖች ላይ ያሳደረው ከፍተኛ ተፅዕኖ ነው፡፡ በመሆኑም ለችግሩ መፍትሔ የሚሰጥ፣ ለምክክርና ለጋራ ልማት ዕቅድ የሚያወጣ አንድ የጋራ ተቋም በማስፈለጉ የየሀገራቱ የውሀ ሀብት ሚኒስትሮች ተሳባስበው ይህን ተቋም እውን አደረጉ፡፡ የተቋሙ ዋነኛ መርህም ለጋራ ራዕይ ስኬት የዓባይን ውሀ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ለጋራ ልማት በማዋል የየሀገራቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኑሮ በተሻለና በፅኑ መሠረት ላይ በመመሥረት በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የሚገኙ ህዝቦች አስተማማኝና ቀጣይነት ያለው ኑሮ እንዲኖሩ ማስቻል ነው፡፡ በቃ!! የኢኒሼቲቩ አጠቃላይ ዓላማና መርህ፣ ሰምና ወርቁ ይኸውና ይኸው ነው፡፡ ፈረንጆች “Win- Win!!” የሚሉት የጋራ ተጠቃሚነት መርህ፡፡

ነገር ግን ይህ የተፋሰሱ አካባቢ አገራትን የጋራ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መርህ፣ ይህ የየሀገራቱን የጋራ ህልውና የሚያበስር መርህ፣ ይህ የህዝቦችን በጋራ ራዕይ ላይ የተመሠረተ አንድነትን እና ትብብርን የሚያጠናክር መርህ የሁሉንም አገራት የጋራ ይሁንታ ሳያገኝ ቀርቶ እነሆ ላለፉት አሥርት ዓመታት ሳይፀድቅ ቆይቷል፡፡ ይህ ብቻም አይደለም፤ ሰነዱ በተቻለ ፍጥነት ፀድቆ ወደተግባር ሊቀየር ሲገባው በአንዳንድ ሀገራት የተሳሳተ አመለካከትና አቋም የተነሳ አሁንም አወዛጋቢነቱ ቀጥሏል፡፡ ለዚህ

አወዛጋቢነቱም፣ አሁን ባለው ተጨባጭ እውነታ፣ ግብፅና ሱዳን የግምባር ቀደምነቱን ሥፍራ ያለተቀናቃኝ ይዘዋል፡፡

ይሁንና በእኩልነት ላይ የተመሰረተውንና የውሀውን አጠቃቀም ፍትሀዊነት የሚያረጋግጠውን መርህ/ሰነድ የተፋሰሱ አምስት ሀገሮች (ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ሩዋንዳና ታንዛንያ) ለጋራ ልማት ይውል ዘንድ በፊርማቸው በማረጋገጥ ህብረትን ፈጥረዋል፡፡ እነዚህ አገራት ቀደም ሲል በቅኝ ገዢዎች ኢፍትሀዊ በሆነ መንገድ የተነጠቁትን መብቶቻቸውን የሚያስመልሱበት አንዱ መንገድ ከመሆኑም በላይ፤ በቅኝ ገዢዎች የተሸረበውን ሴራና ኢፍትሃዊ ውል በማስቀረት የናይል ወንዝ ፍትሃዊ ተጠቃሚነታቸውን በፊርማቸው በአደባባይ አረጋግጠዋል ፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ ሱዳንና ግብፅ ለምን ከዚህ ውል አፈገፈገና ወይም ውሉን ላመፈረም አሳማኝና ተጨባጭ ምክንያታቸው ምንድን ነው? ይህ ነው የወቅቱ አጠያያቂ ምናልባትም እንቆቅልሹ ጥያቄ፡፡

ባጭሩ ጉዳዩን ለማስታወስ ይረዳን ዘንድ ታሪክን በማጣቀስ እንደሚከተለው እንመልከተው፡፡

እንደሚታወቀው የ1959 ዓ.ም ስምምነት ከላይ የተገለፁትን የናይል ተፋሰስ አገሮችን ተጠቃሚነት ያላረጋገጠ/ያገለለ፣ እነዚህ ሀገራት ምንም ዓይነት ድርሻ ከክፍፍሉ እንደሌላቸው (እንዳይኖራቸውም) ታስቦ የተቀረፀ፣ በአንፃሩ የግብፅንና የሱዳንን ሁለንተናዊ ጥቅም ለማስጠበቅ በተለይም በእንግሊዝ ጋሻ ጃግሬነት የተዘጋጀ ‹‹ስምምነት›› ነበር፡፡

ይህም ከዓባይ የውሃ መጠን የአንበሳውን ድርሻ (85%) የያዘችውን ኢትዮጵያን በአንድ ሊትር የውሀ ተጠቃሚነት ደረጃ ላይ እንኳን ያላሰፈረና ከባለድርሻነትና ከተጠቃሚነት ሙሉ በሙሉ ያገለለ አስገራሚ የ "ስምምነት" ሰነድ ነው፡፡

ይህ ሰነድ ነው እንግዲህ ዛሬ ግብፅና ሱዳንን በዓባይ ውሀ አጠቃቀም ላይ ራሳቸውን ብቻ ወሳኝ እንደሆኑ አድርገው እንዲቆጥሩ ያደረጋቸው፡፡

በ1959ኙ ስምምነት የተለየ አቋም ያላቸው አገሮች አንድ የጋራ ራዕይ ነድፈው በጋራ ለማከናወን እያሳዩት ያለው ተነሳሽነት፣ ያወጧቸው ዕቅዶች፣ ዕቅዶቻቸውን ለማከናወን ያስችላቸው ዘንድ እያደረጉት ያለው ቅደመ ዝግጅት ወዘተ ግብፅንና ሱዳንን ያስደሰተ አይመስልም፡፡ በዚህም ምክንያት ይመስላል የተበደሉ ሀገራትን ድምፅ ለመስማት የተሳናቸው ወይም ለመስማት ያልፈለጉት፡፡

ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ኢትዮጵያ፣ ተወደደም ተጠላም፣ ተፈጥሮ ያጐናፀፈቻትን የአንበሳውን ድርሻ የያዘች የውሃው ዋና መገኛና ምንጭ ሀገር ነች፡፡ ከውሃው ፍትሃዊ አጠቃቀም አኳያም በአሁኑ ሰዓት በኤሌክትሪክ ኃይል፣ በመስኖ ልማትና በተፋሰሱ አካባቢ የሕዝቦቿን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ  ያጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅዶችን አዘጋጅታ በመተግበር ላይ ትገኛለች፡፡ ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የነበረውንና ልማዳዊ አስተሳሰቦችን መሠረት ያደረገውን፣ በ21ኛው ክፍለዘመን መነፅር ሲታይና በአሁኑ የፍትሀዊነት ሚዛን ሲመዘን እጅግ ጊዜው ያለፈበትን የስምምነት ሰነድ ተቀብላ ለመቀጠል ትቸገራለች፤ አግባብነትም አይኖረውም፡፡ ይህም ነው ኢትዮጵያን በናይል ቤዚን ኢኒሼቲቭ ሂደት ውስጥ ፍትሀዊ የውኃ አጠቃቀም ይኖር ዘንድ ቁልፍ ሚና እንድትጫወት ያደረጋት፡፡

የናይልን ወንዝ የውሀ አጠቃቀም የሚደነግገውን የ1959 ሰነድ እንኳን አሁን ላይ ሆኖ ያኔም ቢሆን በቅንልቦን ለተመለከተው በየትኛውም መመዘኛ የትክክለኛነት መሠረት ቀርቶ መልክም የለውም፡፡ ባጭሩ ‹‹እናንተ እለቁ እኛ እንጥገብ ወይም እንኑር›› ነው መልዕክቱ፡፡ ይህ ደግሞ በአሁኒቱ ኢትዮጵያ ባጠቃላይም በተፋሰሱ አገሮች ፍፁም ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ያላትን የሰውና የተፈጥሮ ሀብት በመጠቀም ከድህነት መላቀቅና በሚቀጥሉት ቅርብ ዓመታትም መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የሚያስችላትን የልማት ስትራቴጂ አውጥታ ወደ ተግባር የገባችና በመልማት ላይ ያለች ሀገር በመሆኗ ነው፡፡ ይኸው ነው ጉዳዩ፡፡ በአጭሩ የ1959ኙ ውሳኔ ፍትሃዊነት የጐደለው ነበር ብሎ መደምደም ቀላል ይሆናል፡፡

ቅድም Win-Win ያልነውን እንድገመው፡፡ በዓባይ የውኃ አጠቃቀም ላይ የኢትዮጵያ አቋም አንድ ነው፡፡ የዓባይን ውሀ ‹‹በጋራ ራዕይ ላይ ተመሥርቶ ለጋራ ጥቅም ማዋል›› የሚል፡፡ ይህ የማያሻማ፣ ሀቅ እና ግልፅ አቋም በተቃራኒው የተሰለፉ ወገኖችን አይታያቸውም፡፡ ይህ ሀቅ፣ ይህን መሠረት ያለው እውነት፣ ይህን የህዝቦች ድምፅ ለምን ሊገነዘቡት፣ ሊቀበሉት እንዳልቻሉ ለጊዜው ግልፅ አይደለም፡፡ እነሱ የያዙት አቋም ‹‹ሁላችንም›› የሚል ሳይሆን ‹‹እኛ ብቻ ጠቃሚዎች እንሁን›› የሚል ግትርና ፍትሃዊነት የጐደለው አቋም ከመሆን አይዘልም ወደፊት (ምናልባትም በቅርቡ) ጊዜ የሚፈታው ቋጠሮ ይሆናል፡፡

ይህን በወቅቱ ከነበረው የኢ-ፍትሀዊ የውሃ ድርሻ ክፍፍል አንፃር በመመልከት ምን ያህል ኢ-ፍትሃዊነት እንደሚንፀባረቅበት ባጭሩ የሚቀጥለው ታሪክ እንመልከት፡፡

ሱዳን የ1929ኙ የውሀ ክፍፍል ስምምነት እንደገና እንዲታይ ጠይቃ ከብዙ ድርድር በኋላ ( እዚህ ጋ ግብፅን ልብ ይሏል) በ1959ዓ.ም አዲስ የውሀ ክፍፍል ስምምነት ተደረገ፡፡ ለሱዳን አራት ቢሊዮን ሜትር ኩብ ለግብፅ ደግሞ 48 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሀ እንዲደርሳቸው የተደረሰበት የ1929 ስምምነት በ1959 እንደና ተሸሽሎ ቀርቧል፡፡ የ"ተሻሻለው"ም ስምምነት ለሱዳን 18 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ሜትር ኩብ፣ ለግብፅ ደግሞ 55 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ሜትር ኩብ ድርሻን ሰጠ፡፡ ወደፊትም እንደ ዝናቡና በአስዋን ግድብ እንደሚጠራቀመው የውሀ መጠን የግብፅ ድርሻ በአማካኝ 84 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ድረስ ሊስተካከል እንደሚችል ተደርጐ ተወሰነ፡፡ ለኢትዮጵያስ? ምንም፡፡ ለምን? እንድገመው - ለምን?? ለሶስተኛ ጊዜም እንድገመው - ለምን? ሌላም ጥያቄ እናስከትል- እስከመቼ?

ባጠቃላይ በዚህ አጭር ፅሁፍ ያቀረብኩትን በሚከተሉት ሃሳቦች አጠቃልላለሁ፡፡ የዓባይ ውሀ ለጋራ ጥቅም መዋል ይገባዋል፡፡ ኢትዮጵያም የባለቤትነቷን ያህል ባይሆንም እንኳን እኩል ተጠቃሚነቷን የሚከለክላት ምንም ዓይነት ኃይል ሊኖር አይገባም፡፡ ሌሎች እየጠገቡ ኢትዮጵያውያን የሚራቡበትና በዓለም ላይ በድህነት መሥመር መለኪያነት የሚፈረጁበት ዘመን ጊዜው ካለፈ ሰነባብቷል፡፡ ነገሩ ሁሉ እስከዛሬ ድረስ ‹‹የምንጩን ባለቤት ውሃ ነፈጉት›› ሆኖ ቆይቷል፤ ‹‹የዓባይን ልጅ ውኃ ጠማው›› እንዲሉ በመሆኑም ሁለቱም ማለትም መከልከሉም ሆነ መጠማቱ እዚሁ ላይ ሊቆም ሁኔታዎች ግድ ይላሉ፡፡ ባለንበት ክፍለ ዘመን አተያይ "ለኔ ብቻ" የሚለው ፍልስፍና አያስኬድም፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግሥትና ህዝብ እንዲሁም የተፋሰሱ ሀገራት በያዙት የፍትሀዊነት ጥያቄና አቋም ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ ጊዜው አሁን ነው!!!